“የእምዬን አሻራ”

የኢትዮጵያ ህዝብ “እምዬ” ብሎ የሚጠራቸው አፄ ምኒሊክ አስተዋይ ጀግና እንደነበሩ አለም የመሰከረው ሀቅ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ የእምዬ ምኒሊክ ጠላቶች “ ቀን የሰጠው ቅል ዲንጋይ ይሰብራል” እንዲሉ ማንነታቸውን ለማድበስበስና ለመካድ ሲዳዳቸው እናስተውላለን። ነገር ግን አፄ ምኒሊክ ታሪካቸውን እንዳይደበዝዝ አድርገው ስለሰሩት የመላው የጥቁር ህዝብ አርማ ሆነው ይቀጥላሉ። እምዬ ምኒሊክ ከ ١٥٥ ዓመት በፊት ለአባ ጅፋር በላኩት መልዕክት “ ይድረስ ለአባ ጅፋር፤ የሰው ባሪያ የለውም። ሁላችንም የእግዚአብሔር ባሮች ነን። እግዚአብሔር መርጦ ከሰው አልቆ ሲያስገዛ መጨከን አይገባም። ለሰው ቢያዝኑ እድሜ ይሰጣል። ድሀ በተመኘው ይኑር።” እንዳሉ ታሪክ ይመሰክራል። ዛሬ በእኛ ዘመን ፀረ አፄ ምኒሊክ ገዥዎቻችን እነአብይ አህመድ በበታችነት ስሜት እየተሰቃዩ፣ በያዙት ስልጣን ትልቅ መሆን ስለተሳናቸው ስንቱን እንዳፈናቀሉት፣ ስንቱን እንደገደሉት፣ ስንቱን ጅብ እንዳሰበሉት ቤት ይቁጠረው።

እምዬ ምኒሊክ፣ ስመጥሩ ጀግና

ስሙ አይደበዝዝም፣ ሞቶም ባለዝና

አታሎ የገባው፣ አዲሱ መንግሥት

መሪ ቃሉ ጥፋት፣ ማታለል ውሸት

ምኒልክን መፍራት፣ ህዝቡንም መጥላት

ከቶ አይሆንለትም፣ በአድዋ መኩራት።

እንደአለመታደል፣ በስም ብልፅግና

አየን በእኛ ዘመን፣ በስልጣን ብልግና

ምኒሊክን ማድነቅ፣ ማክበር የተሳነው

አሁን የሚያደርገው፣ በተግባር ያየነው

ሁሉም የምኒሊክ፣ መሆኑን አይርሳው

ጀግናው የሰራውን፣ እንዳቅሙ ሳይሰራ

ዋሽቶ የሚያጣላ፣ ጀሌ እያሰማራ

ሸኔ የሚያስጨፈጭፍ፣ ህዝብን በገጀራ

አብይና አዳነች፣ ሽመልስ ቀጀላ

ከነ ጀሌዎቹ፣ ሁሉም በጠቅላላ

የምኒሊክ ጠላት፣ ንጉሱን የጠላ

በቤቱ እንዳይገኝ፣ የሙዚቃ ሸክላ

ፓሊስንም ይተው፣ ይበቃዋል ሸኔ

እቤቱ ይታመም፣ ሆስፒታል ለምኔ

መድሐኒት አይግዛ፣ የእምዬን አሻራ

ምኒሊክን መጥላት፣ ነውና ኪሳራ

ባህር ዛፍ አይቁረጥ፣ ሊታጠን ካሰበ

መሆን ስላለበት፣ ጥላቻና ጥቅም እየተናበበ

መኪናም አይንዳ፣ አይጫማ ጫማ

ባቡር ላይ አይውጣ፣ አይግባ ሲኒማ

ብስክሌት አይንዳ፣ ባባዶ እግሩ ይጓዝ

ብዙ ትውስታ አለው፣ የጥላቻ መዘዝ

ባንክም አይጠቀም፣ በጨው ይገበያይ

ገንዘብና ባንኩ፣ በምኒሊክ ይለይ

ጋዜጣም አያንብብ፣ ህትመት የተባለ

በውሸቱ ትርክት፣ ይኑር እየማለ

ሚንስትርም አይሹም፣ እንደምኒሊክ

ጥቅማ ጥቅሙ ይቅር፣ የኤለክትሪክ

ባረመኔ አገዛዝ፣ ይበቃል ትርክት

እርግፍ አርጎ መተው፣ ከጠሉ ላይቀር

ማረጋገጫ ነው፣ ቃልን በተግባር።

ነገር ግን ሁሉንም፣ መተው ካቃታችሁ

የእመዬ መሆኑን፣ እኔ ላስታውሳችሁ።

ዘውዲቱ የማነ

2023-02-28